# ግድብ ወይስ ዝርፊያ አለገደብ?

ከመዝገበ ባየህ

አምባገነኖች ዕድሜያቸው የሚረዝምበት አንዱ ምክንያት በሀሰታቸው የሚታለል ዜጋ ሲበዛና ውዥንብርም ሲሰፍን ነው። ጨቋኝና ክህዲ ቡድን ሀገር ወዳድ መስሎ ሲለፍፍ የሚያምኑትን ካገኘ በለስ ነጋ ጠባ ይቀናዋል። ወያኔ ሀፍረተ ቢስ ዋሾ ነውናም ዛሬ ቢነቃብትም ርዕስ እየቀያየረ በርካታዎችን ማወናብዱ አልቀረም። ከሻዕቢያ ጦርነት ሲገባ የሚጠላትንና የሚያጠቃትን ኢትዮጵያ የሚወድ መስሎ በጎኑ ስንቶችን አሰልፎ አስፈጅቷል። ወያኔ አስብን "ሊያስመልስልን" ብለው ያመኑም ነበሩ። የዘንድሮው ማወናበጃ ደግሞ ሕዳሴ ግድብ ምስረታ የሚባለው ነው።

በአባይ ላይ ይሰራል የተባለው ግዙፍ ግድብ ሕዳሴ የሚል ስያሜ በወያኔ ተሰጥቶታል። በወያኔ ለኢትዮጵያ ሕዳሴ ይመጣ ይመስል! ግድቡ በጣም ግዙፍ ሲሆን የአካባቢውን ዜጎች ከቀዬአቸው የሚያፈናቅል ነው። ወደ 5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ይጠይቃል-- በብር ምንዛሪው በጣም አስደንጋጭ ነው። ይህ ገንዘብ ከውጭ ሊገኝ ባለመቻሉ ዜጎች ከወያኔ ቦንድ እንዲገዙ በመገደድ ላይ ናቸው። የወያኔ ደጋፊዎች--ሆዳሞችና የክልል አንድ ተወላጆች--እየገዙ/እየከፍሉ

ናቸው። ባለሐብት (ባለሆቴል፤ንግድ፤ወዘተ) የተባሉትም በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ ለወያኔ አምጡ አዋጡ እጅ ሰጥተዋል ። ብልጡ ወያኔ የሕዝብን ዕይታ ከሕዝባዊ አመጽ ወደ ግድብ ለመውሰድ አቅዶ፤በግብጽ ላይም አረፋ ደፍቆ ሲያሾፍ ያመኑትና ይህ ጉዳይ ሀገራዊ ግዳጅ ነው ብለው የወያኔን ሰበካ ያስተጋቡ አሉ። ከስሜታዊ አቅዋም ባሻገር ግን ይህን የወያኔ ግድብ እውን ለህገር ይጠቅማል?

1. በመጀመሪያ ደረጃ ግዙፍ ግድብ መስራት ለአከባቢ ደህንነት በጣም ጎጂ ተብሎ ብዙ ሀገሮች ትተውታል።
2. በኢትዮጵያ ዛሬ ያሉት ግ.ድቦች ( ለገዳዲ፤ቆቃ፤ ጣና በለስ፤ ግልገል ጊቤ 1 ፤ ግልገል ጊቤ 2-- በመሰራት ላይ ያለው ግልገል ጊቤ 3 ን ሳይጨምር) ለመላ ኢትዮጵያ በቂና የሚተርፍ የመብራት ሀይል ሊሰጡ የሚችሉ ናቸው)። ቻይና ጉቦ ሰጥቶ ወታትሮ የሰራው የተከዜም ግድብ ቢሆን በመጠኑ ሀይል ያመርታል።
3. ሌላ ግድብ በአሁኑ ጊዜ በጣም አጣዳፊና አስፈላጊም አይደለም ማለት ይቻላል። በሌለ ገንዘብ ሕዝብን ለጭንቅ ዳርጎ መሰራት ያለበትም አይደል። ባለው ሀይል ተጠቅሞ መብራት በፈረቃን ማከተም ሲቻል ይህ ያልሆነበት ምክንያት ወያኔ ለጅቡቲ መሸጡ ላይ እንጂ መብራት ማዳረሱ ላይ ምንም ትኩረት ባልመስጠቱ ነው።

4. የወያኔን የዘረፋ ዕቅድ መደገፍ ብሔራዊ ግዴታ ነው ሊሉን የተነሱት ወያኔዎች አወናባጆች ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገሩ ባለቤት ሲሆን አቅሙን መጥኖና በችሎታው/ ልክ አስፈላጊ ግድቦችን ሆነ ሌሎች ዕቅዶችንም ከግብ ያደርሳል። ግልገል ጊቤ 3 ሆን ሕዳሴ ግድብ አካባቢውን የሚበክሉ፤ ሕዝብን የሚያፈናቅሉ፤ መላ ሕዝብን ለወያኔ ዝርፊያ የሚያጋልጡ ናቸው።

5. ሕዝብ ቦንድ የሚገዛው መንግስት የተባለው ታማኝ በሆነበት ሁኔታ ነው። ወያኔ የወሮበላዎች ጥርቅም ነው። ከወያኔ ቦንድ መግዛት ማለት ፍየልን ከነብር ጎራ መደበቅ ነው። ኪሳራ!

6. ሕዳሰ የተባለው ግድብ ለወያኔ ዝርፊያ ይመቻል እንጂ ግድቡ የሚሰራራ የሚጠናቀቅ አይሆንም። ለምን ቢባል

ሀ/ ለግድቡ የሚያስፈልገው ገንዘብ በሕዝብ ሊዋጣ የሚችል አይደለም።

ለ / ወያኔ የራሱ ወታደራዊ የንግድ ተቋም ለግድቡ አስፈላጊ የሆኑትን አምስት ግዙፍ ተርባይኖች መስራት አለበት ስላለና ተቋሙም ይህ ችሎታ ስለሌለው ግንባታው በአያሌ ዓመታት የሚጓተት ይሆናል።

ሐ/ ወያኔ የስልጣን ዕድሜው አጭር ነውና የግድ ቡን ፍጻሜ የሚያይ አይሆንም።

መ/ ወያኔ ዋና ዓላማው ግድብ ግንባታ ሳይሆን በግድብ ሽፋን መረን የለቀቀ ዝርፊያ ማካሄድ ነውና ነው።

የሕዝብ ዕይታና ትኩረት ወደ አመጽ እንዳይሆን ወያኔ ግድብ የሚል ማደናገሪያ አመጣ። ዛሬ ደግሞ ኣኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን ድንጋጌዎች አውጣልሁ እያክ ነው። ሌሎች ደግሞ የአጨቃጫቂ ህብረት ስምሪት ርዕስ  ከፍተው ዜጎች በአመጹ ላይ ሳይሆን በሌላ ጉንጭ አልፋ ንትርክ እንዲጠመዱ አድርገዋል። ሕዳሴ ተብዬው ግድብ ሀገራዊ ጉዳይ ሳይሆን የወያኔ የዝርፊያ ዘመቻ ነው። ለዚህ ተባባሪ መሆንና  ገንዘብ መለገስ  ተወደደም ተጠላም ሀገርን ጎጂ ድርጊት ነውና ሰበብ እየደረድሩ ለወያኔ በግድብ ግንባታ ሰበብ የሚረዱ ሁሉ ሀገርን እየጎዱ መሆኑን ማውቅ ይገባችዋል። የሚገነባ ግድብ የለም — የሚዘረፍ ዜጋ ግን ሞልቷል። እስከመቼ ነው በወያኔ የምንወናበደው?